## በሐኪም የታዘዙልዎትን የዓይን መነፅሮችን መጠቀም እና መንከባከብ

**(USING AND CARING FOR YOUR PRESCRIPTION EYEGLASSES)**

ለመጀመሪያ ጊዜ የዓይን መነፅሮችን እያገኙ ከሆነ ወይም የሐኪም ትእዛዝዎን እየቀየሩ ከሆነ፣ አይኖችዎ ከአዲሶቹ ሌንሶች ጋር እንዲላመዱ ከ2 እስከ 3 ሳምንታት ይጠብቁ። መጀመሪያ አካባቢ መጠነኛ ማዞር፣ ራስ ምታት ወይም ትንሽ የማቅለሽለሽ ስሜት ሊሰማዎት ይችላል። ጭን ወለሉ ከወትሮ ይበልጥ የቀረበ ወይም የራቀ ሊመስል ይችላል። እነዚህ የሕመም ምልክቶች ያልተለመዱ አይደሉም። Seattle/King County Clinic መነፅሮችን እንደገና መስራት አይችልም።

## ለመነፅሮች እንክብካቤ ማድረግ

- በማያደርጉበት ጊዜ መነጽርዎን በማስቀመጫው ውስጥ ያስቀምጡት
- መነጽር ሲያደርጉ እና ሲያወልቁ በሁለቱም እጆችዎ ይሁን
- መነፅሮችን በሳሙና እና በውሃ ያጽዱ እናም በደንብ በውሃ ያስለቅቁ
- መነፅሩን በስላሳ ጨርቅ ያድርቁ
- አስፈላጊ ከሆነ በአካባቢው የሚገኝ ኦፕቲካል ሱቅ መነጽርዎን እንዲያስተካክል ያድርጉ (ብዙውን ጊዜ ያለምንም ክፍያ)

## የማንበቢያ መነፅሮች (ለቅርብ እይታ ብቻ)

- የእይታ ስራን (ማንበብ፣ መስፋት፣ መጻፍ፣ ወዘተ.) ሲሰሩ ብቻ ያድርጉት።
- አድርጎ ከቦታ ቦታ መራመድ አይመከርም

## ባይፎካል መነፅሮች (ለሩቅ እና ለቅርብ እይታ)

- አዲሶቹን ሌንሶች እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ ለመልመድ ሁልጊዜ መነጽርዎን ይልበሱ
- መነጽር ሲያደርጉ፣ ለርቀት እይታ በቀጥታ ወደ ፊት ይመልከቱ
- መነፅሮችን አድርገው ጭንቅላትዎን ወደታች እያዘንበሉ። ይልቁንም በማንበቢያ ቦታ ሌንሶች በኩል ለማየት ዓይኖችዎን ብቻ ወደ ታች ያንቀሳቅሱ
- ለርቀት፣ ወለሉን ሲመለከቱ ወይም ደረጃዎችን ሲወርዱ አገጭዎን ወደ ደረትዎ በትንሹ ያስጠጉ ይህም የሌንሶች በርቀት ቦታ በኩል እየተመለከቱ ነው